
# Man and Sin



## ሰው እና ኃጢያት

በክርስቲያናዊ አስተምህሮ
አገልግሎት

TCM

## መግቢያ

በዚህ ኮርስ ውስጥ ሁል ጊዜ በሰዎች ሕይወት ውስጥ የሚነሱ የተለመዱ ጥያቄዎችን ለመመለስ ይረዳል። በተለይም

- እኔ ማነ ነኝ ?
- ከየት መጣሁ ?
- ለምንድር ነው የምኖረው ?
- ከሞት በኋላ ምን እሆናለሁ ?

የሚለት ነገሮች ትክክል አሊያም ትክክል ባለሆነ መልኩ በሰዎች አእምሮ ውስጥ ሊቀመጡ ይችላሉ፤ በመሆኑም እነዚህን ጥያቄዎች በተገቢው መንገድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ በሆነ መልኩ መመለስ እና ማሳየት የዚህ ኮርስ ዓላማ ነው።

# ማውጫ

1. አስተምህሮ ሰብዕ....................................................................3

1.1. የመንደርደሪያ ሐሳቦች ....................................................................3

1.2. የሰው - መነሾ/መገኛ ....................................................................6

2. የሰው ተፈጥሮ ....................................................................10

2.1. ሰው-በእግዚአብሔር መልክ እና ምሳሌ መፈጠሩ ......................................10

2.2. የእግዚአብሔር መልክ በሰው መሆኑ ያለው ነባራዊ እንድምታ ....................12

2.3. የሰው ሁልንተናዊ ተፈጥሮ ....................................................................14

3. ኃጢያት እና ውጤቱ ....................................................................17

3.1. ኃጢያትን አስመልክቶ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ ................................17

3.2. የኃጢያት ውጤት ....................................................................20

3.3. የኃጢያት ሽፋን እና ጥልቀት ....................................................................21

3.4. የኃጢያት ማኅበረሰባዊ ገጽታ ....................................................................23

4. ተያያዥነት ያላቸው አመለካከቶች እና ሐሳቦች ...............................25

4.1. ኢ-ክርስቲያናዊ አመለካከቶች ....................................................................25

4.2. ከኃጢያት ጋር የሚያያዙ ሐሳቦች ....................................................................27

4.3. የሰው ፍጻሜ ....................................................................29

5. ማጠቃለያ....................................................................31

# 1. አስተምህሮ ሰብዕ

## *1.1 የመንደርደሪያ ሃሳቦች*

### *1.1.1. የዚህ ጥናት መሰረት*

✓ የዚህ ኮርስ ርዕስ “ሰው እና ኃጢያት” የሚል ነው ፤ይህም ሰው የሚለው ቃል የሚወክለው በጾታ ተለይተው ያሉትን ወንድ እና ሴት የሆኑ ሰዎችን ሁሉ በአንድት ነው።

በመሆኑም ሰውን በሁለት ትልልቅ ደረጃዎች ውስጥ መመደቡን ነው የምናጠናው

1ኛው - በእግዚአብሔር ፍጥረት በነበረው በመጀመሪያው ደረጃ ሲሆን / ሰው ፍጹም ንጹህ ሆኖ በነበረበት የሕይወት ደረጃ /

2ኛው - ደግሞ ከውድቀት በኋላ ባለው ደረጃ ነው። ባለመታዘዝ ምክንያት ኃጢያትን ሰርቶ በነበረበት የሕይወት ደረጃ

✓ ሰውን ለማጥናት የምንቀርብበት መንገድ ስነመለኮታዊ አቀራረብ ነው በመሆኑም በሁለት ነጥቦች ላይ መሰረት ያደረገ ነው

1ኛው - ሰው ከፈጠረው ከፈጣሪ ጋር ካለው ግንኙነት አንጻር ፤ በመሆኑም ልክ እንደ ታሪክ ፣ ባዮሎጂ፣ ሳይኮሎጂ እና ሶሶሎጂ ሰው ከራሱ ጋር ወይም ከራሱ መሰል ጋር ባለው ግንኙነት ላይ የተመሰረት አይደለም በመሆኑም ጥናቱ ምሉዕ የሆነ እይታን ይሰጠናል።

2ኛው - ሰውን በሁለንተና ይዘቱ ነው የምናጠናው - አካላዊውን ፣ ስነ-ልቦናውን እና ማሕበራዊ እንቅስቃሴውን ለይተን እና ገንጥለን አይደለም።

✓ ሥነ መለኮታዊ በሆነ መልኩ ማጥናት ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ ማጥናት እጅግ የተለያዩ ነገሮች ናቸው ቢሆነም ቅሉ ሳይንስ እና ነገረ መለኮት አይጣሉም ። ይልቁን ነገረ መለኮት እና ፍልስፍና ይጋጫሉ እንጂ።

### *1.1.2. የዚህ ጥናት አስፈላጊነት*

✓ ለገዛ ራሳችን የመንፈሳዊ ሕይወት ጥንካሬ/ዕድገት

- በእግዚአብሔር መልክ እና አምሳል መፈጠራችን ስናውቅ እና ስንረዳ ለተሻለ መንፈሳዊ እድገት ፣ ወደ ክርስቶስ ሙላት ለመድረስ ጥረት እናሳያለን

✓ አለም አቀፍ ኢ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ የአስተምህሮ ተግዳሮቶችን ለመከላከል/ አቃቤ እምነትን ለማዳበር/

- ከሳይንስ የሚመጡ ሙግቶችን ለማሸነፍ ( ለምሳሌ - በብልቃጥ ስለ ሚፈጠሩ ልጆች)
- ከሰው ልጆች የሚመነጩ ልዩ ልዩ አስተሳሰቦች - ለሰው ልጆች የተዛባ አመለካከትን ያዳብራሉ ( ለምሳሌ - አዶልፍ ሂትለር ለጀመርን ዜጋ ያለው የተለየ ከበሬታ፣ ዘረኝት ፤ አጥፍቶ መጥፋት )
- እድሜ ጠገብ ከሆኑ ሃይማኖቶች የሚመነጩ አስተምህሮዎች ( ለምሳሌ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ፣ ሂንዱይዝም ….ወዘተ)

✓ በሰዎች መካከል ትክክለኛ ግንኙነትን ለማሳደግ

- በእግዚአብሔር መልክ እና አምሳል ከተፈጠረ ሁሉ ጋር እንደ ጠላት አድርገን ከምናስባቸው ጋር እንኳን ላይ የሚኖረን አቋም ( ወደዱ…በእግዚአብሔር መልክ ተፈጥረዋልና)
- ከጋብቻ አንጻር ወንድ እና ሴት አድርጎ እግዚአብሔር የፈጠረበትን ዓላማ በውል እንድንገነዘብ ያደርገናል። በመሆኑም የተመሳሳይ ጾታ ጋብቻን እንድንጸየፍ እና የእግዚአብሔር ዓላማ እንደሌለተበት ትክክልኛ ግንዛቤን ይሰጠናል።
- የጾታ የበላይነት አስተሳሳተበ ከተሳሳተ ጉድጓድ የሚመነጭ ሃሳብ መሆኑን እንድንገነዘብ ያደርገናል። በመሆኑም የወንድ የበላይ ሲቀጥልም የሴትን የበላይነት ለማረጋገጥ ፌሜኒዝም ለመመሰረት ከመነሳት ይጠብቀናል።

### *1.1.3. የተበላሹ ወይም የተሳሳቱ አመለካከቶች የሰው ተፈጥሮን አስመልክቶ*

- *ሰው ማሺን ነው* - ከዚህ የሚመነጨው ውጤት ሰውን በማንነቱ ሳይሆን የሚመዝኑት በሚሰሩት ነው። በመሆኑም በስራቸው ይከበራሉ ፣ ይሰገድላቸዋል..ወዘተ።
- *ሰው እንስሳ ነው* - አካላዊ ይዘቱ ከእንስሳት ጋር የሚመሳል ነገር ቢኖረውም በዓይነቱ ግን ፈጽሞ ከእንስሳ የተለየ ነው። ደግሞም ሰው እንስሳ አይደለም።
- *ሰው በወሲብ ስሜት/ኃይል የሚነዳ ፍጡር ነው* - የኦስትሪያ ተወላጅ የሆነ የስነ ልቦና ሊቅ ነኝ ባይ ሲግሙንድ ፍሩድ የሚባለው ሰው ስለ ሰው ያለው ፍልስፍና ሰው በውስጡ በሚነዱት

ኃላይ የሚንቀሳቀስ ነው። ከእነዚህም መካካል ደግሞ ዋነኛው የወሲባው ፍላጎቱ ነው። የሰው አጠቃላይ ባህርይ የሚቆጣጠረው ይኸው የወሲብ ፍላጎቱ ነው፡

- *ሰው አምራች ኃይል ነው* - ይህ አስተሳሰብ በኮሚኒዝም ሥርዓተ ማሕበረ ውስጥ ሰርጾ የነበረ ነው። ሰው ቁሳካላዊ ነው በመሆኑም ሰው የሚያስፈልጉት ሶስት መሠረታዊ ነገሮች ናቸው (ምግብ ፣ ልብስ፣ መጠለያ) ።

- *ሰው የተፈጥሮ ድንገተኛ ክስተት ነው* - ከሰው ልጅ ከእውቀት ምጥቀት ጋር ተያይዞ የመጣ አስተሳሰብ ነው። ምክንያቱም ስለ ሕዋ ምርምር ባረደገበት ዘመን ሰው እራሱን እጅግ በጣም ትልቅ አድርጎ ያስብ ነበር። ወደ ሕዋ የተደረጉት ጎዞዎች እና ምርምሮች ግን ከሚታየው እና ሊደረስበት ከማይችል ግዙፍ ዓለም ጋር ሰው ሲነጻጸር እጅግ እጅግ በጣም አናሳ በመሆኑ ምክንያት ሰው ድንገት የተገኘ ነው ወደ ሚል ድምዳሜ እራሳቸው አድርሰዋል። እውነቱ ግን ይህ አይደለም።

- *ሰው ለራሱ በራሱ የሚኖር ነው* - ሰው የተፈጥሮ ድንገተኛ ክስተት ነው የሚለውን ሐሳብ የተቀበሉ ሰዎች የመኖር ዓላማ እና ትርጉሙ ስለሚጠፋባቸው የራሳቸውን ሕይወት ትርጉም ለመስጠት ሕግ እና ደንብ እንዲሁም በሕብረተሰብ መካካል ሊመራ የሚችል ማህብረሰባዊ እሴቶችን በራሱ ቀርጾ መጓዝ ይችላል የሚል ስሜትን የሚያንጸባርቁ ናቸው።

- *ሰው ውስጠ አልቦ ነው* - ይህ አስተሳሰብ የሚመነጨው ካለይ የተዘረዘሩትን ሀሳቦች ሁሉ መሰረት ያደረገ በመሆኑ እና የእግዚአብሐርን ሕልውና የማይቀበሉ ሰዎች የሚያራምዱት ሃሳብ ነው። ለምሳሌ ቡዲዝም "ሰው ምንም ዓይነት ሊሞት የማይችል ሰብዕና የለውም" ፣ "ሁሉም የሰው ልጅ ፍላጎቶች ክፉ ናቸው" እንዲሁም ሰው ነፍስ እንዳለው አይቀበሉም። ከሞት በኋላ ሕይወት የሌለው ሰው ሲሞት ሞተ በሰበሰ ወይም ተቃጠለ በቃ ተደመደመ።

### *1.2. የሰው - መነሻ/ መገኛ*

#### *1.2.1. ኢ- ክርስቲያናዊ አስተምህሮ የሰው መገኛን አስመልክቶ*

- *ፓንቴስቲክ አመለካከት* - ፓንቴይስቲክ "ሁሉ እግዚአብሔር ነው" "እግዚአብሔር ሁሉም ነገር ነው" ብሎ የሚያስብ አመለካከት ያላቸው ናቸው። እግዚአብሔርን ከፍጥረቱ ለይ ላለማሰብ

የሚያስችል አመለካከት ሲሆን በአሁኑ ዘመን ከአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው።

- *ርደምታዊ አመለካከት* - ሰው የተፈጠረው በዝግመተኛ ሂደት ነው።በመሆኑም ተፈጥሮ በራሷ ሕግ ከቀላል ወደ ውስብስብ ወደ ሆነ እድገት ደረጃ መጥታለች የሚሉ ናቸው። ርደምታዊ አመለካከት በሁለት የተከፈለ ነው።
    - *ተፈጥሮአዊያን* - አስቀድም እንዳልነው ተፈጥሮ በራሷዋ ሕግ በረጅም ጊዜ ኅዙ ከቀላል ወደ ውስብስብ እድገት መታለች።
    - *ቴሰቲካዊያን* - የተፈጥሮ ሕግ ሳይሆን ከርደምታዊ ሂደት ጀርባ ያለው ራሱ እግዚአብሔር ነው ብለው የሚያስቡ ናቸው።

### *1.2.2. መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ የሰው አፈጣጠርን አስመልክቶ*

- *ሰው ድንቅ የእግዚአብሔር ፍጥረት ነው* - መጽሐፍ ቅዱሳችን ስለ ሰው ተፈጥሮ የሚያስተምራቸው ድንቅ ድንቅ የሆኑ አስተምህሮዎች አሉት። ከእነዚህም መካከል የተወሰኑት እንመልከት።

ዘፍ 1፡26 እግዚአብሔርም አለ፦ *ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር የባሕር ዓሦችንና የሰማይ ወፎችን፥ እንስሳትንና ምድርን ሁሉ፥ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ይግዙ።*

27 *እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው።*

ዘፍ2፡7 እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ።

ዘፍ 2፡21 እግዚአብሔር አምላክም በአዳም ከባድ እንቅልፍን ጣለበት፥ አንቀላፋም ከጎኑም አንዲት አጥንትን ወስዶ ስፍራውን በሥጋ ዘጋው።

22 እግዚአብሔር አምላክም ከአዳም የወሰዳትን አጥንት ሴት አድርጎ ሠራት ወደ አዳምም አመጣት።

ኢዮ10፡8 እጅህ ለወሰችኝ ሠራችኝም ከዚያም በኋላ ዘረህ ታጠፋኝ ዘንድ ፈለግህ።

33፡4 የእግዚአብሔር መንፈስ ፈጠረኝ፥ ሁሉንም የሚችል የአምላክ እስትንፋስ ሕይወት ሰጠኝ

መዝ100፡3 እግዚአብሔር እርሱ አምላክ እንደ ሆነ እወቁ እርሱ ሠራን እኛም አይደለንም እኛስ ሕዝቡየማሰማርያውም በጎች ነን።

ኢሳ45፡12 እኔ ምድርን ሠርቻለሁ ሰውንም በእርስዋ ላይ ፈጥሬአለሁ እኔ በእጄ ሰማያትን ዘርግቼአለሁ፥ ሠራዊታቸውንም ሁሉ አዝዣለሁ።

ኤር27፡5 ምድሪቱን በምድርም ፊት ላይ ያሉትን ሰዎችንና እንስሶችን በታላቅ ኃይሌና በተዘረጋችው ክንዴ ፈጥሬአለሁ ለዓይኔም መልካም ለሆነው እሰጣታለሁ።

ሚል2፡10 ለሁላችን አንድ አባት ያለን አይደለምን? አንድ አምላክስ የፈጠረን አይደለምን? የአባቶቻችንን ቃል ኪዳን ለማስነቀፍ እኛ እያንዳንዳችን ወንድማችንን ስለ ምን አታለልን?

የሐዋ17፡24 ዓለሙንና በእርሱ ያለውን ሁሉ የፈጠረ አምላክ እርሱ የሰማይና የምድር ጌታ ነውና እጅ በሠራው መቅደስ አይኖርም፤

25 እርሱም ሕይወትንና እስትንፋስን ሁሉንም ለሁሉ ይሰጣልና አንዳች እንደሚጎድለው በሰው እጅ አይገለገልም።

26-27 ምናልባትም እየመረመሩ ያገኙት እንደ ሆነ፥ እግዚአብሔርን ይፈልጉ ዘንድ በምድር ሁሉ ላይ እንዲኖሩ የሰውን ወገኖች ሁሉ ከአንድ ፈጠረ፥ የተወሰኑትንም ዘመኖችና ለሚኖሩበት ስፍራ ዳርቻ መደበላቸው። ቢሆንም ከእያንዳንዳችን የራቀ አይደለም።

ራዕ 4፡11 አንተ ሁሉን ፈጥረሃልና ስለ ፈቃድህም ሆነዋልና ተፈጥረውማልና ክብር ውዳሴ ኃይልም ልትቀበል ይገባሃል እያሉ በዙፋኑ ፊት አክሊላቸውን ያኖራሉ።

- *ረጅም የመሬት እድሜ ሙግት፡-* ሰው በስድስተኛው ቀን እንደ ተፈጠረ ምንም እንኳን መጽሐፍ ቅዱስ ቢናገረም ይህ ግን መቼ እንደነበር ማወቅ ያስቸግራል ይህንን አስመልክቶ ምድር ረጅም እድሜ አላት በሚለው እሳቤ (ከዘፍ 1-5 ባለው ንባብ መሰረት) ሰውም በምድር ላይ መኖር ከጀመረ ብዙ እድሜ አለው የሚሉ ሰዎች እንደ ጀምስ አሸር (1581-1656) ሳንይንሳዊ መረጃዎችን ያቀርባሉ።

✓ ለምሳሌ ፡-

  - እንደ ትውልድ ዘገባ። ይህም የትውልድ ዘገባ በዘፍጥረት መጽሐፍ ላይ ተገልጦአል፤ እንዲሁም የተዘለሉ ሰዎች እናዳሉም በዘፍጥረት እና በሉቃስ ወንጌል መካከል እንኳን ልዩነትን ማስተዋል ይቻላል።

  - ተጨማሪ ምላምቶች
    - ቴስቲክ ርደምታዊ ምላምት (There is God after evolution)
    - የምድርን ፊት የቀየረው የጥፋት ውሃ ነው እንጂ ምድር ረጀም እድሜ የላትም ፤
    - እያንዳንዱ የፍጥረት ቀን ረጅም ታሪካዊ ጊዜ እንጂ 24 ሰዓትን አይወክልም ፤
    - እግዚአብሔር ሰውን ከመፍጠሩ ደቀም ብሎ ዓለማትን ፈጥሮአል፤
    - በዘፍጥረት 1፡1 እና 1፡2 መካከል ረጅም የጊዜ ክፍተት አለ፡

☞ *በጥቅሉ የሰውን ልጅ የፍጥረት ጊዜ ለመለካት የትውልድ ዘመን ዘገባ፣ሌሎች ምላምቶችን መከተሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ጋር ሊጋጠም ስለ ማይችል መከተል አይቻልም።*

### 1.2.3. *ሰው ሰው ሆኖ በመፈጠሩ ሊያመጣ የሚችለው እውነት*

- *የፈጣሪው ጥገኛ መሆኑ* ፡- ይህ ሀሳብ ለማለት የተፈለገው እራሱ በራሱ ብቻ ያለምንም እና ማንም ረዳት መኖር አይችልም ለማለት ነው። በመሆኑም ሰው ለመኖር አምላክ ያዘጋጀቸው ነገሮች ያስፈልጉታል። መዝ139፡13፤ ኢሳ42፡5፤ ኢዮ33፡4 በመሆኑም ሰው ለመኖር የአምላክ ቸርነት ያስፈልገዋል ፤ በመሆኑም እነዚህን ነገሮች በውስጣችን ስንገነዘብ ሊፈጥርልን የሚችለው እውነት
  - ✓ የእግዚአብሔር የፈጣሪያችን ጥገኛ መሆናችንን እውቅና መስጠትን - ኢሳ64፡4፤ መዝ23፡1፤ በመሆኑም ስለ ፈቃዱ ልንጠይቅ እና ወደ እርሱ ልንጸልይ እንጀምራለን። ማቴ6፡10፤26፡39
  - ✓ በሞቀ እና በተነሳሳ ስሜት ተገቢ ምላሽ ለእግዚአብሔር መስጠትን - በእርሱ ሥራ መደነቅን ፤ ማመስገንን መዝ139፡14፤
  - ✓ እጅግ ትሁት በሆነ ልብ በአምላካችን በእግዚአብሔር ፊት መሆንን - መዝ8፡4

- *ሰው ከተቀሩት ፍጥረታት ጋር ያለው የጠለቀ ዝምድና* - ከምድር ላይ ፍጥረታት ጋር በአንድ ቀን መፈጠሩ፣ እርሱም እንደ እንስሳቱ ከምድር መፈጠሩ፣ እግዚአብሔር በፈጠረው ኤደን ገነት መቀመጡ እና እንዲንከባከባቸው መታዘዙ ወይም ኃላፊነት መቀበሉ፤ ይህ የፍጥረት ሂደት ግንኙነቶች በሰው ልጆች ላይ የሚፈጥሩት እንድምታ አለው ይኸውም
  - ✓ አግባብነቱን የጠበቀ ግንኙነትን አሊያም መስመሩን የጠበቀ ውህደት እንዲኖረው፤
  - ✓ ተገቢ የሆነ አክብሮት እና ጥንቃቄ ለእግዚአብሔር ፍጥረት መስጠትን፤ ዘፍ9፡2-3
  - ✓ ከፍጥረት አካሔድ ልንማራቸው የሚገቡ መልካም ሥነ ምግባራት - ምሳ6፡6

- *ልዩ ፍጡር መሆኑ* ፡- በእርግጥ እግዚአብሔር ሁሉን የፈጠረ ቢሆንም ሰው ግን ከፍጥረቱ ሁሉ ልዩ ነው፤ምክንያቱም በራሱ በእግዚአብሔር መልክ እና ምሳሌ መፈጠሩ።
  - ✓ ከፍተኛ የሆነ የእውቀት ፣ የስሜት እና የመንፈሳዊ ፍላጎት ያለው
  - ✓ ሊጠፋ የማይች ውስጣዊ ማንነት ያለው (ነፍስ መንፈስ)፤
  - ✓ ነጻ የምርጫ ፈቃድ ያለው ነው
- ውስንነትን የተላበሰ ፍጡር መሆኑ ፡- የሰው ልጅ የሚኖርበት ዘመን (በጊዜ በሰዓት) ፣ የአእምሮው ገደብ እና በቦታ የተወሰነ ወይም የተገደበ ፍጡር ነው።

### *1.2.4.* የሰው ዘር አንድነት እና ልዩነት

- አንድነቱ
  - ✓ ከአንድ ሰው መገኘታቸው
  - ✓ ተመሳሳይነት ያለው አካላዊ ይዘት መያዛቸው
  - ✓ ተመሳሳይነት ያለው ማህበራዊ ግንኙነቶች መያዛቸው
- ልዩነቱ
  - ✓ የቋንቋ ብዛት ( በሰዎች ልጆች ስህተት የተሰጠ ፍርድ)
  - ✓ የባህል ልዩነቶች
  - ✓ የቀለም ልዩነት

❖ *በእርግጥ እግዚአብሔር በአንድነታችን ውስጥ ያለውን ልዩነት ይወዳል፡፡ ይህም ልዩነት እስከ ለዘላለም የሚቀጥል አይደለም ነገር ግን አንድ ቀን ተመልሰን ፍጹም ወደ ሆነው አንድነት እንመለሳለን፡፡*

# 2. የሰው ተፈጥሮ

### *2.1 ሰው- በእግዚአብሔር መልክ እና ምሳሌ መፈጠሩ*

እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር በመልኩ እና በአምሳያው ነው፤ በመሆኑም እግዚአብሔር እንደ ሰው የሚታይ አካላዊ አቋም የለውም ዮሐ4፡24 በተመሳሳይ መልኩ ሰው እንደአምላኩ መልክ እና ምሳሌ መፈጠሩን የሚገልጡ መንፈሳዊ ገጽታ፣ እውቀት (አእምሮአዊ) ፣ መልካም ግብረገባዊ ገጽታዎች አሉት።

#### *2.1.1 መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃዎች*

*ሊጤኑ የሚገባቸው መሰረታዊ የምንባብ ክፍሎች* - (ዘፍ 1፡26-28፤ ኤፌ4፡22-25፤ ቆላ3፡9-10)

- *ዘፍ1፡26-28* - በዚህ ሃሳብ መሰረት የሚከተሉትን ሀሳቦች ማለት እንችላለን ከፍጥረት ሁሉ የሚለይበት ገጽታ ሰው እንዳለው መረዳት እንችላል “መልክ እና ምሳሌ” በሚለው ቃል ውስጥ፤ በፍጥረቱ ሁሉ *የመግዛት እና የማስተዳደር* ኃላፊነት፤ሴት እና ወንድ ሆነው በጾታ ተለይተው ተመሳሳይ የእግዚአብሔርን መልክ እና አምሳሌ ማባዘት እንዲችሉ መሆናቸው።
- ኤፌ4፡22-25 - በዚህ ክፍል ሃሳብ መሰረት የእግዚአብሔር መልክ እና ምሳሌ *ጽድቅ እና ቅድስና* የሞላበት ሕይወት እንደ ሆነ ግልጽ ተደርጎአል።
- ቆላ3፡9-10 - በዚህ የምንባብ ክፍል ውስጥ የእግዚአብሔር መልክ የሚለውን ሀሳብ ለመግለጥ በፍጹም በሚታደስ *ሰማያዊ እውቀት* መሆኑን ተገልጾአል።

*“መልክ” እና “ምሳሌ” ያላቸው የትርጓሜ ስሜት*

“ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን” የሚለው ቃል - በእርጋት ከተመለከተው የሚያመላክተው ሐሳብ
መልክ - ንግግር እና ምክንያታዊ መሆንን ሲሆን፤በዕብራይስጥ “Tselem” – Image
አምሳያ - ደግሞ ሥነ ምግባራዊ ባሕርያትን አመላካች ነው። በዕብራይስጥ “Demuth” – Likeness

#### *2.1.2 መልክ እግዚአብሔር ባህሪያት*

- *ወሰኝ ገጽታዎች* - በዚህ ሐሳብ ውስጥ ልንጠቀልላቸው የሚገቡ ነገሮች
  1. የንግግር ክህሎት - ከምድር ፍጥታት ሁሉ ሰው ብቻ ነው ይህ ክህሎት ያለው ሃሳብን የማቀናጀት የመግለጥ
  2. ምክንያቲያዊ መሆን እና ነጻ ምርጫ የማድረግ - ሰው ከፍጥረቱ ነገሮች በምክንያት የማድረግ እና ያለማድረግ ሰብዕናን የተላበሰ ነው።

3. ሰው አዳዲስ ነገሮች የመፈጥር ክህሎት ያለው ነው - እንደ እግዚአብሔር የሌለን ነገር መፍጠር ሳይሆን ያለን ነገር በተለያየ መልክ የሞቅረጽ እና የማሳደግ ክህሎት ያለው ሰው ብቻ ነው።
4. ሰው ፍጥረትን የመጠበቅ እና የማስተዳደር ችሎታ ያለው ነው- ዘፍ1፡28 ነገር የሰው ልጅ ይህንን ለማድረግ

ሀ. እርሱ ራሱ ለእግዚአብሔር በቅድሚያ ሲገዛ ነው፤

ለ. ባለአደራነት የሚሰማው እና ለአዳዲስ ነገሮች ፈጠራ እራሱን ሲያዘጋጅ ነው፤

- *ሥነ ምግባራዊ ገጽታዎች*

የእግዚአብሔር መልክ እና ምሳሌ የሚባሉትን ሐሳቦች ከኤፌ4፡23፤ ከቆላ3፡9-10 መሰረት

1. እውቀት - በቅድሚያ እግዚአብሔርን ከማወቅ ይጀምራል ከዚያም ሌላው ይቀጥላል
2. ጽድቅ እና ቅድስና - መዝ45፡7 1ጴጥ1፡15-16

### *2.1.3 መልከ እግዚአብሔር በሰው ሕይውት ውስጥ ያለው ተዛምዶ*

እግዚአብሔር አንድ አምላክ ሆኖ ነገር ግን በሰስት አካል የሚኖር በመካከላቸው ግልጽ የሆነ ተዛምድ ያላቸው ናቸው፡ ፡ ሰውም በእግዚአብሔር መልክ እና አምሳል የተፈጠረ በመሆኑ

1. *ያታዊ ግንኙነት ላይ* - የእግዚአብሔር አምሳል የሆኑ ሌሎች ልጆችን ለመውለድ ለመባዛት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ አንድ አካል ለመሆን ነው።
2. *እኩልነት ላይ* - ሰው ሁሉ በእግዚአብሔር አምሳል በመፈጠሩ ምክንያት አንዱ ታላቅ አንዱ ደግሞ ታንሻ አይደለም።የትኛውም ሰው ከየትኛውም ሰው የተለየ ነገር የለውም። ጌታ ሁሉንም ሰው ድሃ ሐብታም ኃጢያተኛ ጻድ ቅ ሳይል በእኩል ደረጃ ሁሉን አገለገለ። በወንድ እና በሴት መካከል በሥራ የመጣ ልዩነት ካልሆነ በተስተቅር የማንነት ልዩነት ጨርሶ የለም።

### *2.1.4 ትክክለኛው የእግዚአብር መልክ መገለጫ - ኢየሱስ*

የእግዚአብሔርን መልክ በትክክል እና በግልጽ ያሳው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። ቆላ1፡15 ዕብ1፡3 ዮሐ1፡18፤14፡9

- ✓ ትክክለኛ የባሕርይው መገለጫ
- ✓ ለሰው ልጆች የእግዚአብሔርን መልክ ያሳየ

- ✓ ክርስቶስን በመምሰል የእግዚአብሔርን መልክ መመለስ ይቻላል የሚልን መልዕክት ያሳየ፤

## *2.2 የእግዚአብሔር መልክ በሰው መሆኑ ያለው ነባራዊ እንድምታ*

### *2.2.1 ነባራዊ ሐቆች*

1. ከእግዚአብሔር ጋር ፍጹም የሆነ ተረአክበ ለማድረግ
2. ከሰው ሁሉ ጋር መልካም ህብረት ለማድረግ/ ባህል ዘለል ግንኙነቶችን ለማድረግ
3. ለደህንነት/ የሰው ሕይወት ክቡር መሆኑን ለማሳየት
4. በሰዎች መካከል የእኩልነት ሚዛንን እንዲኖር አስችሎአል
5. የጣዖታትን ትክክለኛ ገጽታ እንድንገነዘብ አስችሎአል
6. የእግዚአብሔርን የፍጥረት ባለቤትነት ሰው እንዲረዳ አስችሎአል
7. ሰው የሚሰራውን ሥራ ሁሉ በአግባቡ እንዲመዝን አችሎታል

### *2.2.2 የእግዚአብሔር መልክ እና ማህበራዊ/ህብረተሰበአዊ ሥርዓት*

ሰው ሲፈጠር እግዚአብሔር በራሱ አምሳያ ፈጠረ ስንል በመልካም ስነ ምግባራዊ ገጽታው እንደሆነ ተመልክተናል በመሆኑ ሰው በማህበራዊ ኑሮ ውስጥ ይህንን ማንነቱን የሚያንጸባርቁ ስርዓት አለው

1 *በቤተሰብ መካከል* ፡- ምስዋዕትነትን የሞላበት ፍቅር ፣ እርስ በርስ ለመገዛት የሚያስችል መንፈስ ፣ የአክብሮት ልብ በአንድ ቤተሰብ መካከል የሚገለጡ የእግዚአብሔር መልክ ገጽታዎች ናቸው። (ኤፌ5፡1፤21-6፡ ቆላ3፡18-21 ዘዳ6፡6-7፤ ምሳ22፡6)

2 *በመንግስት ደረጃ* ፡- እግዚአብሔር ሕዝብ በአግባቡ እንዲተዳደሩ ይሻል በመሆኑም ስልጣንን ለሰው ልጆች ይሰጣል ክፉዎችን የሚበቀልበትም መንገድ ነው። በመሆኑም ሰው ሁሉ ለባይ ባለስልጣናት የመገዛት አሊያም የመታዘዝ ኃላፊነት አለበት። ሮሜ13፡1-5

3 *በቤተ ክርስቲያን ውስጥ* ፡- ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ዘላለማዊ እቅድ የተመሰረተች ናት። በመሆኑም በክርስቶስ የፍቅር ዋጋ ላይ የበቀለች እንደሆነች ሁሉ አማኞች እግዚአብሔርን በፍቅር እንዲታዘዙት እና እንዲወዱት እንዲሁም እርስ በርሳቸው በፍቅር እንዲዋደዱ የሚል የእግዚአብሔር መልክ ገጽታ የሚገለጥበት መንገድ ሆኖአል።

- ❖ *የመንግስት እና የቤተ ክርስቲያን ግንኙነት- መንግስት የእግዚአብሔርን ፍትህ በጽድቅ እስካገለገለ ድረስ የእግዚአብሔር እጅ ይሆናል ቤተ ክርስቲያንም በቅድስና እና በጽድቅ መንገድ የእግዚአብሔርን መልክ ማሳየት አለባት ይህ ሲሆን የእግዚአብሔር ሃሳብ በእነርሱ ይፈጸማል።*

### 2.2.3 የሰው ውድቀት ውጤት እና ተጽዕኖው

ሰው እግዚአብሔር አምላኩን ባለመታዘዙ ምክንያት የኃጢያት ባሪያ ሆኖአል። አዳም ይህን በማደረጉ ምክንያት በሰው ልጆች ላይ የደረሰው የመጀመሪያው ውጤት

- ❖ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው ፍጹም ሕብረት ተበላሸ
- ❖ ብዙ መልካም እድሎችን እና ጥቅሞችን አጥቶአል
- ❖ ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆኑ ቅጣቶች አግኝተውታል ( እርግማን ፣ ሞት)
- ❖ በሰብዕና ላይ የታዩ ለውጦች ነበሩ። ይህን ለውጥ ሰዎች በሁለት ጎራ ተከፍለው ይመለከቱአቸዋል።

#### 2.2.3.1 ሁለት ዓይነት አመለካከቶች

1. የእግዚአብሔር መልክ በሰው ውስጥ ሙሉ በሙሉ የለም
2. የእግዚአብሔር መልክ በከፊል ተጎድቶአል

| **ሙሉ በሙሉ ተበላሽቶአል** | **መልካም ምግባሩ እና መንፈሳዊነቱ ተጎድቶአል /ድካም/** |
|---|---|
| ❖ መልካም ስነ ምግባራዊ ገጽታውን አጥቶአል | ❖ መልካም የማድረግ ገጽታውን እና ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ሕብረት አጥቶአል። |
| ❖ ሰው በመንፈሱ ሙታን ነው | ❖ ሰው በመንፈሱና በስነ ምግባሩም ደካማ ሆኖአል ነገር ግን አልሞተም። |
| ❖ ወሰኝ ባሕሪያቱ እጅጉን ተጎድተውበታል | ❖ መልካም ለማድረግ በውስጥ አለ |
| ❖ በራሱ ጉልበት ወደ አምላኩ መመለስ አይችልም። እግዚአብሔር ጸጋውን ሊሰጠው ይገባል ለመልካም ስራ። | ❖ በፈቃዱ መልካም ማድረግን ይችላል። |

- አመለካከቶቻችን በወንጌል ስርጭት ላይ የሚያስከትለው ተጽእኖ
  - ○ ሙሉ በሙሉ ተበላሽቶአል ብለው የሚቀበሉ
    1. ሰው ኃጢያተኛ ነውና ለመዳንም ሆነ ለመለወጥ የወንጌል ስብከት ያስፈልገዋል፤
    2. በመንፈሳቸው ሙታን በመሆናቸው ምክንያት በመንፈስ ቅዱስ ድጋፍ ሊደረስላቸው ይገባል
    3. በእርግጥ ሰባኪው ማሳማን አይጠበቅበትም ውስጣቸው መንፈሳዊ መጠነኛ ንቃት ስላለ
  - ○ በጉዳት እና በድካም ነው ያለው ብለው የሚያስቡ ደግሞ
    1. ውስጡ ሙሉ በሙሉ ስላልሞተ ሰባኪው ቀስ በቀስ ወደ በታው ሊመልሰው ይችላል።

2. ሰባኪው ለማሳመን ከመጣር ይልቅ በእምነት ለደካማው ሰው ወንጌልን መስበክ አለበት፡
:

3. ይህንን ሃሳብ የሚደግፉ በተጨማሪ የሚያቀርቡት ከስብከት ይልቅ መልካም ስራን በመስራት መመስከር ይቻላል ይላሉ

4. በዚህ ውስጥ የሚፈለገው ለውጥ ከሌሎች ሃይማኖቶች የተሻሉ ሰዎችን ማፍረት እንጂ የተለወጡ ክርስቲያኖች ማድረግ አይደለም

- *እንግዲህ ለወንጌል ስብከት አገልግሎት አመለካከታችን እጅግ ወሳኝ መሆኑን ነው፤ ምክንያቱም ሰው በራሱ እጅግ መላካም እንደሆነ የምናስብ ከሆነ ወንጌል ለመስበክ ብዙም አቅም የሌለን ስንሆን፤ ሰው ሁሉ ደግሞ ኃጢያተኛ እንደሆነ የምንቀበል ከሆነ ወንጌልን ለመስበክ የተሰጠ ማንነት ይኖረናል።*

## *2.3 የሰው ሁልንተናዊ ተፈጥሮ*

የሰውን ሁለንተና አስመልክቶ  የሚሰጡ ሀሳቦች በሁለት ጎራ የተከፈሉበት ምክንያት እና የሚመነጩት ከመጽሐፍ ቅዱስ የቃላት አገባብ አንጽር መሆኑ እሙን ነው። በመሆኑም መሠረቱን የጠበቀ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥናት ማድረግ ይጠበቅብናል።

### *2.3.1 የሰው ሁለንተና*

መጽሐፍ ቅዱሳችን ነፍስ እና መንፈስ ከሚባሉት ቃላት ባሻገር የተለያዩ ቃላትን በተለዋጭነት እና በራሳቸው ቋሚ መጠሪያ ሆነው የሚያገለግሉ ቃላትን ይጠቀማል። ለምሳሌ ልብ፣ አእምሮ፣ ስጋ እና ሰውነት/አካል በሚሉ ቃላት የሰው ተፈጥሮን ይገልጣል። የሚገልጡትም የሰውን ሁለንተናዊ ተግበር እና ከአምላኩ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት ነው።

1. ሕዝ18፡20 - ሰውን /አንድን ግለሰብ ለመግለጥ
   <u>*"ኃጢአትን የምትሠራ ነፍስ*</u> እርስዋ ትሞታለች ልጅ የአባቱን ኃጢአት አይሸከምም፥ አባትም የልጁን ኃጢአት አይሸከምም የጻድቁ ጽድቅ በራሱ ላይ ይሆናል፥ የኃጢአተኛውም ኃጢአት በራሱ ላይ ይሆናል።" - ሰውን ለመግለጥ ነው።
2. መዝ6፡2-4 - የሰውን አጠቃላይ ሁለንተና ለመግለጥ
   "ድውይ ነኝና አቤቱ፥ ማረኝ አጥንቶቼ ታውከዋልና ፈውሰኝ።ነፍሴም እጅግ ታወከች አንተም አቤቱ፥ እስከ መቼ ድረስ ነው?አቤቱ፥ ተመለስ ነፍሴንም አድናት፥ ስለ ቸርነትህም አድነኝ።"
3. መዝ63፡1 - የሰውን አጠቃላይ ሁለንተናውን ለመግለጥ

"አምላኬ፥ አምላኬ፥ ወደ አንተ እገሠግሣለሁ ነፍሴ አንተን ተጠማች፥ ሥጋዬ አንተን እንዴት ናፈቀች እንጨትና ውኃ በሌለበት በምድረ በዳ።"

4. መዝ73፡21 - የሰውን አጠቃላይ ሁለንተናውን የውስጥ ስሜቱን

"ለመግለጥልቤ ነድዶአልና፥ ኵላሊቴም ቀልጦአልና"

❖ *በአጠቃላዩ እግዚአብሔር ስለ ሰው አጠቃላይ ሁለንተና እንጂ ለመንፈሳዊው ገጽታ ብቻ የሆነ ትኩረት የለውም ለዚህም እንደ መረጃ ማጤን የሚቻለው ደህንነታችን ነው። የሰው ሁለንተና እስኪዋጅ ድረስ መዳናችን ፍጹም አይሆንም።*

### *2.3.2 ሰው ከሁለት ገጽ/ነገሮች ውቅር ነው ( ዳይ ኮቶሚ)*

❖ በዚህ ሀሳብ የሚመላሱ ሰዎች የሚያነሱት ሐሳብ ሰው በሁለት ገጽታዎች ሊገለጥ ይችላል ባዮች ናቸው ፤ ማለትም ሰው ሥጋ እና ነፍስ ያለው ነው።

❖ በእርግጥ ይህ ሀሳብ የሰውን ሁለንተና ከመግለጥ ይልቅ ሰው ከሞት በኋላ ላለው/ለሚኖረው ሕይወት ገለጭ ለመሆን የበለጠ ይጠቅማል። ሰው ሲሞት ስጋው እና ነፍሱ እንደሚለይ መጽሐፍ ቅዱስም ያስተምራል።

### *2.3.3 ሰው ከሶስት ገጽ/ነገሮች ውቅር ነው (ትራይ ኮቶሚ)*

❖ ይህን ሀሳብ ሰው ሶስት የተለያየ ክፍሎ አድረጎ ማሰብ እጅግ ወደ ስህተት ይመራናል።

❖ ነገር ግን የሰው ማንነት ሊገለጡ የሚችሉ ሶስት ገጽታዎች አድርገን ከወሰድን ግን ተገቢ የሆነ ግንዛቤ ይኖረናል።

❖ የሰው ሁለንተናዊ ገጽታዎች

  - ☞ ሥጋ፡- አካላዊ ብሎቶችን ሁሉ ያካተተ
  - ☞ ነፍስ ፡- የሰው ስሜት ፈቃድ እና እውቀት መገለጫ
  - ☞ መንፈስ፡- ክፉ እና ደግ የመለየት (ሕሊና) እና መንፈሳዊ ተረአክበ ተብሎ ሊገለጥ ይችላል።


❖ አንድ ሰው ሥጋዊ ነገር ሲያደርግ ሰውዬው ሥጋው ብቻ አደረገ አይባልም።ሲያመልክም ሰውዬው አመለከ እንጂ መንፈሱ አመለከ አይባልም።

❖ በመሆኑም ሰው አካላዊ፣ ሥነ ልቦናዊ እና መንፈሳዊ ፍላጎት አለው። በመሆኑም ሰው ሰው የሚሆነው ሁለንተናዊው ፍላጎት ሲሟሉለት ብቻ ነው።

  - ☞ በዚህ መሰረታዊ ሀሳብ ውስጥ ልብ ልንላቸው የሚገቡ ጉዳዮች
    - ✓ ሰውን ለመርዳት ስንዘጋጅ በሁለንተናው መሆን እንዳለበት መገንዘብ፤

- ✓ በመንፈሳዊ እና በሥነ ልቦናዊ ፍላጎቶች መካከል መሰረታዊ የሆነ ልዩነቶች እንዳሉ መረዳት
- ✓ ቅድሚያ የሚሠጠው ፍላጎት የትኛው እንደሆነ በውል መገንዘብ (መንፈሳዊው ከሁሉ ቅድሚያ እንደሚገባው መረዳት)

<u>የሰው ገጽታዎች ሶስት ናቸው ብለው የሚቀበሉ ሰዎች ሁለት አመለካከቶች</u>



# 3. ኃጢያት እና ውጤት

### *3.1 ኃጢያትን አስመልክቶ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ*

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኃጢያት ምንነት በግልጥ ያስተምራል። በእርግጥም ይህ ኮርስ ስለ ኃጢያት የበለጠ ግንዛቤ ይሰጠናል።

#### *3.1.1 መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላት ኃጢያትን አስመልክቶ እና እንድምታቸው*

❖ የኃጢያት መንስኤ

የኃጢያት መንስኤን ሊገልጡ የሚችሉ ቃላት አሉ ፤ በእነርሱ ላይ ተመስርተን ስለ ኃጢያት ማጥናት እንጀምራለን።

☞ አለማወቅ (1ጴጥ1፡14፤2፡15 1ቆሮ14፡37-38 ኤፌ4፡18)

☞ ከመስመር ውጪ መሆን ፣ መቅበዝበዝ ፣ መጥፋት (ኢሳ53፡6 1ጴጥ2፡25)

☞ አለመታዘዝ (ሮማ5፡19፤ 2ቆሮ10፡6 ዕብ2፡2-3) - ለመስማት ፍቃደኛ አለመሆን፤ለመቀበል ወይም ለማመን ፍቃደኛ አለመሆን

❖ የኃጢያት ባህሪ

የኃጢያትን ባህሪ ለመግለጥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክፍሎችን መሰረት በማድረግ በትክክል ሊገልጡ የሚችሉ ቃላትን በማየት የኃጢያትን ባህሪ እንመለከታለን።

☞ መተላለፍ - (ኢሳ53፡6፤ መዝ78፡56-57 ዳን5፡27) ይህ ሐሳብ የተሳሳተ መንገድን መያዝ (ኢሳ1፡4፣ 44፡20 53፡6፤ ዘኍ14፡43 ዮሐ14፡6) ፤ ተሰመረውን የምልክት መስመር ውጪ መሆን (መዝ78፡ 65-57፤ማቴ6፡33፤ ሮሜ7፡15-23) ፣ከደረጃ በታች መሆን (መዝ14፡2-3፤ ዳን5፡27፤ ሮማ1፡18 3፡ 23)

☞ እግዚአብሔርን ባለመምሰል ሕይወት መመላለስ- (2ጢሞ2፡16 ቲቶ2፡12 ይሁ18)

☞ ጽድቅ የጎደለው ሕይወት (ሮሜ1፡18 ፤3፡10)

☞ አመጽ ( 2ቆሮ6፡14፤1ዮሐ3፡4)

☞ ኢፍታዊነት (ሌዋ19፡15፤ መዝ82፡2)

☞ ደንዳናነት ( ኢሳ1፡2 1ቲሞ1፡9)

☞ ፍትወት (1ዮሐ2፡16፤ 1ጴጥ4፡2-3)

☞ ክፋት (ማቴ22፡18 ማር7፡23)

❖ የኃጢያት ውጤት

☞ ክፋት (ዘፍ47፡9 አሞ9፡3) - /physical disaster/

- ☞ ድካም (ዘዳ9፡27 ፤ ኢሳ57፡20-21) ግለሰቡን እረፍት ይነሳዋል፤የውስጥ ሰላም ማጣት
- ☞ የበደለኝነት ስሜት (ዮሐ9፡41 1ቆሮ11፡27) - በደለኛው ቅጣት እንደሚጠብቀው ያሳስባል
- ☞ መከራ (ምሳ22፡8) በእርግጥ ሁሉም መከራ ከኃጢያት የመጣ ነው ብሎ ማለት አስቸጋሪ ልሆን ይችላል፡፡

❖ ኃጢያትን አስመልክቶ ከተሰጡት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንታኔዎች

1. እግዚአብሔር ከሰው የሕይወት ደረጃ በታች መሆን ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔር ከሰው ልጆች ከሚፈልገው የኑሮ ዳረጃ በሕጉ ከተገለጠው በታች የመኖርን ሂዳት አመላካች ነው ኃጢያት፡፡ በመሆኑም ከመስመር ውጪ መሆን፣ ተገቢ ያለሆነ ሕይወት/ኑሮ፣ ሕገ ወጥነት ተብሎ ሊገለጽ ይችላል፡፡
2. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኃጢያት በጥቅል/በደፈናው አይናገረም ይልቁን የኃጢያትን መንሰዔ፣ባህሪ፣ ዓይነት እና ውጤት ቁልጭ ባለ መልኩ ያቀርባል፡፡እኛም በስብከታችንም ሆነ በትምህርታችን ይህንን መስመር መከተሉ ተገቢ ነው፡፡

### *3.1.2 ውስን እና ግልጽ የሆኑ የኃጢያት ዝርዝሮች*

የኃጢያትን ዝርዝር አስመልክቶ በአዲስ ኪዳን ወደ አምስት በታዎችን መጠቀስ ይቻላል፡፡

- ✓ ማር7፡21-23 "ከውስጥ ከሰው ልብ የሚወጣ ክፉ አሳብ፥ ዝሙት፥ መስረቅ፥ መግደል፥ ምንዝርነት፥ መጐምጀት፥ ክፋት፥ ተንኰል፥ መዳራት፥ ምቀኝነት፥ ስድብ፥ ትዕቢት፥ ስንፍና ናቸውና፤ይህ ክፉው ሁሉ ከውስጥ ይወጣል ሰውን ያረክሰዋል፡፡"

- ✓ 1ቆሮ6፡9-10 "ወይስ ዓመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዳይወርሱ አታውቁምን? አትሳቱ፤ ሴሰኞች ቢሆን ወይም ጣዖትን የሚያመልኩ ወይም አመንዝሮች ወይም ቀላጮች ወይም ከወንድ ጋር ዝሙት የሚሠሩወይም ሌቦች ወይም ገንዘብን የሚመኙ ወይም ሰካሮች ወይም ተሳዳቢዎች ወይም ነጣቂዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም፡፡"

- ✓ ገላ5፡19-21 "የሥጋ ሥራም የተገለጠ ነው እርሱም ዝሙት፥ ርኵሰት፥መዳራት፥ ጣዖትን ማምለክ፥ ምዋርት፥ ጥል፥ ክርክር፥ ቅንዓት፥ ቁጣ፥ አድመኛነት፥መለያየት፥ መናፍቅነት፥ ምቀኝነት፥ መግደል፥ ስካር፥ ዘፋኝነት፥ ይህንም የሚመስል ነው፡፡ አስቀድሜም እንዳልሁ፥ እንደዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም፡፡"

- ✓ ሮሜ1፡29-31 “ዓመፃ ሁሉ፣ ግፍ፣ መመኘት፣ ክፋት ሞላባቸው፤ ቅናትን፣ ነፍስ መግደልን፣ ክርክርን፣ ተንኰልን፣ ክፉ ጠባይን ተሞሉ፤ የሚያሾከሹኩ፣ሐሜተኞች፣ አምላክን የሚጠሉ፣ የሚያንገላቱ፣ ትዕቢተኞች፣ ትምክህተኞች፣ ክፋትን የሚፈላለጉ፣ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፣”

- ✓ ቆላ3፡5-9 “እንግዲህ በምድር ያሉቱን ብልቶቻችሁን ግደሉ፥ እነዚህም ዝሙትና ርኵሰት ፍትወትም ክፉ ምኞትም ጣኦትንም ማምለክ የሆነ መጎምጀት ነው።...አሁን ግን እናንተ ደግሞ ቍጣንና ንዴትን ክፋትንም፥ ከአፋችሁም ስድብን የሚያሳፍርንም ንግግር እነዚህን ሁሉ አስወግዱ።እርስ በርሳችሁ ውሸት አትነጋገሩ፥ አሮጌውን ሰው ከሥራው ጋር ገፋችሁታልና፥”

በእነዚህ ዘርዝሮች ውስጥ ልብልንል የሚገባው ነጥብ አብሮ ተመልክቶአል።

- ✓ ኃጢያት እራሱን በተለየየ መልክ መገልጥ ይችላል፤
- ✓ ኃጢያተኛ ሰው ወደ እግዚአብሔር መንግስት መግባት አይችልም፤
- ✓ አንዳንድ ኃጢያቶች ከሌሎች ይልቅ የመዛመት ባህሪ ያላቸው አሉ፤
- ✓ ኃጢያት የሰው አጠቃላይ የሕይወት ገጽታን ይጎዳል፤

### *3.1.3 የኃጢያት ተፈጥሮ እና ምንጩ*

በመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ እና ገለጣ መሰረት ኃጢያት “መጥፎ” ነገር ከሚባለው ሀሳብ የዘለቀ ነው። ለዚህ ደግሞ እንደ ምክንያት የሚጠቀሱ ጉዳዮች አሉ

1. *ኃጢያት “ድርጊት ብቻ” ሳይሆን የሰው ሁናቴ መሆኑ፤* ይህ በጳወሎስ አስተምህሮ መሰረት በኤፌ2፡1-2 “በበደላችሁና በኃጢያታችሁ ምክንያት *ሙታን* ነበራችሁ” የሚል ገለጣ ተሰጥቶታል።እንዲሁም በሮሜ7፡ 5፤18፡25 መሰረት ደግሞ “ተሸናፊ ማንነት” “sinful nature” በመሆኑም እንደ በሽታ ሊገለጥ ይችላል ምክንያቱም በሽታ የተለያየ ምልክቶች አሉት ተመሳሳይ ምልኩ ኃጢያት እራሱን በተለያዩ ክፉ መንገዶች እራሱን ይገልጣል(ማር7፡21-23)። በእግጥም ኃጢያት የሰው ልጆች የልብ ዝንባሌ ነው።
2. *ጅማሬው ያለው መሆኑ፤* በዘፍ1፡31፤3፡1-19 መሰረት ሰው ከንጽህና ሕይወት ወደ ተሸናፊነት ሕይወት ወረደ። ነገር ግን በእግዚአብሔር ፍጥረት መጀመሪያ ምንም ዓይነት ክፋት አልተፈጠረም ሁሉም እጅግ መልካም ነበር።
3. መነሸው በሰው ፍቃድ ውስጥ መሆኑ፤ ሰው በኃጢያት የወደቀው የተሰጠውን ነጻ የምርጫ ፈቃድ መለማመድ በጀመረበት ሰዓት ነው። በኃጢያት ትርጉምም ውስጥ እንደ ምንገነዘበው “አመጽኝነት” 1ዮሐ3፡4 ማለት እሺ አለማለት ነው።

4. ከአንዱ ሰው መመንጨቱ፤በሰው ታሪክ ውስጥ የኃጢያት ጀማሪ አዳም ነው፡፡ በመሆኑም ከአንዱ ከአዳም የሸንፈት በር ለሁላችን ተከፈተ፡፡በመሆኑም ሰው ሁሉ በኃጢያት ኃይል ላይ ጉልበት አጣ ረዳትም ፈላጊ ሆነ፡፡ መልካም ብቻ የማድረግ አቅሙ ክፉ በሚያደርግ አቅሙ ተበላሸ፡፡

## 3.2 የኃጢያት ውጤት

### 3.2.1 ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ባለው ግንኙነት

- *መወቀስ* - ማንም ሰው ውሸት ሲናገር የኃጢያተኝነት ስሜት ይሰማዋል፡፡ እንዲሁም በግላችን ብንዋሽ ሂላናችን እረፍት ይነሳል፡፡
- *የእግዚአብሔር ቁጣ* - በኃጢያቱ የተወቀሰ እና ኃጢያተኝነቱ የተሰማው ሰው ሁሉ በእግዚአብሔር ቁጣ ሥር ነው ያለው፡፡ ዮሐ3፡36 ሮሜ1፡18 2፡5 9፡22 ይህም የእግዚአብሔር ቁጣ ከእግዚአብሔር የቅድስናው ባህሪ ከኃጢያት ጋር ባለመጋጠሙ የሚነሳ ነው፡፡
- *ቅጣት* - ኃጢያት ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ፍርድ ወይም ቅጣትን ያመጣል፡
  - ✓ ቀጥተኛ ያልሆነ ስንል ተፈጥሮአዊ የሆኑ ሂደቶች የሚያመጡብን ማለታችን ነው፡፡ ለምሳሌ- በዝሙት ምክንያት የኤች አይ ቪ ሕመምተኛ መሆን፣ ለተለያዩ የአባላዘር በሽታዎች መጋለጥን፡፡ በንዴት እና በቁጣ ምክንያት የጨጓራ ህመም፣ የአእምሮ ህመም እና ሌሎችም፡፡ 2ሳሙ12፡7-12 ገላ6፡7-8
  - ✓ ቀጥተኛ ስንል ከእግዚአብሔር ዘንድ በእግዚአብሔር እቅድና አጀንዳ መሰረት ጊዜውን ጠብቆ ሁሉም ሰው እንደስራው ይከፈለዋል፡፡2ሳሙ12፡14 የሐዋ5፡1-10
- *ሞት* - የመጀመሪያም የመጨረሻም የኃጢያት ውጤት ነው፡፡
  - ✓ መንፈሳዊ ሞት - ከእግዚአብሔር መለየት
  - ✓ አካላዊ ሞት - ነፍስ እና መንፈስ ከሥጋ መለየት
  - ✓ ዘላለማዊ ሞት - ለዘላለም ከእግዚአብሔር መለየት የሰው ልጆች የመጨረሻ ቅጣት፡፡

### 3.2.2 በራሱ በሰው ላይ

- *ከእውነትን መሸሽ* - ሰው እውነት ከተቀበለ ከፍተኛ ወቀሳ ስለ ሚገጥመው እና ለሠራውም ጥፋት ብይን እንደ ሚሰጠው ስለ ሚረዳ ከእውነት ይሸሻል፡፡ ዮሐ3፡20
- *የኃጢያትን ህልውና መካድ* - የኃጢያትን ህልውና የሚክድ የእግዚአብሔርንም ሕልውና ወደ መካድ ለመሔድ ቀላሉ መንገድ ነው፡፡ በመሆኑም የጥፋተኝነት ስሜትን ለማጥፋት የሚደረግ የመጀመሪያ እርምጃ ነው፡፡
- *እራስን ማታለል* - ይኸውም ራሳቸውን ያጸድቃሉ (ትክክል ነኝ ባይነትን ማስፈን ይጀምራሉ) ኤር17፡9 ፣ እራስን ከሌሎች ጋር ማነጻጸር ፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የራስን ስህተት/ጥፋት ባለማየት

የሌሎችን ኃጢያት በማጉላት ማቴ 7፡3-5 ፣ ለጥፋቶቻችን የማይመጥናቸው ጥሩ ስያሜን በመስጠት (ለምሳሌ - ለስድባችን "እኔ ፊለፊት ተናጋሪ ነኝ" በሚል ሽፋን መስጠት።) መዝ139፡ 23-24

- *መደንዘዝ* - (1ጢሞ4፡2 ፤ ሮሜ1፡21 ፤ ኤፌ4፡19) ምንም ስለ መልካም እና ክፉ ተገቢ የሆነ ስሜት ማጣት። የተዛባ አመለካከት ስለ እሴቶች ያለው ሰው ባህሪ ነው።
- *እራስ ወዳድነት* - ከትዕቢ ወይም ከኩራት የሚመነጭ ነው።ከልክ ያለፈ ለራስ የሚሰጥ ሚዛን ነው። ኤፌ4፡17-5፡2

### 3.2.3 በሰዎች መካከል ባላቸው ግንኙነት

- *ውድድር* - የመጥፎ ግንኙነት መነሾ ነው። ይህም ደግሞ ሰዎች ውድድርን ለራሳቸው ጥቅም ማስገኛ አድረገው ከወሰዱት ማለት ነው።ያዕ4፡1-3 2ቆሮ10፡12 ለትክክለኛ እና ለጤነኛ ውድድር መለኪያው ክርስቶስ ብቻ ነው።
- ለሌላው አለማሰብ - በእርግጥ የዚህ ክፋት ስሩ ለራስ ከማሰብ ብዛት የሚመጣ ነው። በጥሩ ጎኑ ምሳሌ የሚሆነን ሳምራዊው መንገደኛ ምሳሌ ነው።ሉቃ10፡30-37
- *የሌሎችን ማንነት ለግል ጥቅም ማዋል* - የሌሎች ድካም ፣ ማጣት ፣ ማግኘት ለራስ ጥቅም ማዋል። የራስን ስም ለማስጠራት መጠቀም ፤ ትልቅ እና ጥሩ ሰው ሆኖ ለመታያ የሌሎችን ድካም መገልገል።

### 3.2.4 በዓለም ላይ

- የተፈጥሮን ሚዛን ያዛባል - እጅግ መልካም የነበረው ዓለም ክፉት የሞላበት ሆነ። ዘፍ1፡31 ዘፍ3፡ 17-19
- ፈጣን የሆነ ለውጥን ያመጣል - ሞት እና እርግማን ወደ ሰው ልጆች ሁሉ ደረሰ።ዘፍ2፡17 3፡2-3፤ 19
- ልዩ ልዩ ጥፋቶችን ያስከትላል - የመሬት መንቀጥቀጥ፣ የመሬት መንሸራተት፣ እሳተ ጎመራ፣ አውሎ ንፈስ ፣ርሃብ፣ ጎርፍ፣ አጥፊ ትንኞች (የወባ፣ የእህልን ሁሉ ጨምሮ)፣

## 3.3. የኃጢያት ሽፋን እና ጥልቀት

### 3.3.1 ሽፋኑ

- ብሉይ ኪዳናዊ አስተምህሮ

በእግዚአብሔር ፊት ማንም ኃጢያት ያልሰራ ንጹህ ሰው የለም። 1ነገ8፡46፤መዝ143፡2፤ መክ7፡20 በእግዚአብሔር መንገድ የሄዱ መንፈሳዊ ሰዎች ቢኖሩም ከኃጢያት ጋር መታገላቸውን እግዚአብሔር አከበረላቸው እንጂ ከኃጢያት ፍጹም ነጻ ነበሩ ማለት ግን አይደለም። (ለምሳሌ፡- ሄኖክ፣ ኖሕ፣ አብርሃም ፣ ኢዮብ፣ ዳዊት ወዘተ)

☞ አዲስ ኪዳናዊ አስተምህሮ

ሰው ሁሉ ኃጢያተኛ እንደ ሆነ እና የእግዚአብሔርም ክብር እንደ ጎደለው በግልጽ ያስተምራል። ሮሜ3፡9-18 ይሁን እንጂ አዲስ ኪዳን ኃጢያተኛ ነው ብቻ ብሎ አያበቃም ነገር ሰው ሁሉ መዳንን ማግነት እንዳለበት እና ሁሉም በአንዱ በአዳም አለመታዘዝ ደግሞ ሞት እንደደረሳቸው ይገልጻል።

### *3.3.2 ጥልቀቱ*

✓ አጠቃላይ ጥፋት

- አጠቃላይ ጥፋት ማለት ምን ማለት ነው
    - *የሰውን ማዕከላዊ ክፍል አበላሽቶአል* - የሰው ማዕከላዊ ክፍል ነው የምንለው "ልብ" ነው። የሕይወት መውጫ ከእርሱ ነውና ለብህን አጥበቀህ ጠብቅ። ልብ የሰው ማዕከላዊ ክፍል ነው (ማር7፡21-23) ከዚህ የተነሳም ኃጢያት የሰው ልጆች ሁለተኛ ተፈጥሮ እስኪመስል ድረስ ሆኖአል ምክንያቱም ሰው ሁሉ ሊለየው እና ሊወገድ የማይቻል በሕርይው መስሎታል።
    - *የሰው አጠቃላይ ሁለንተናን አበላሽቶአል* -
        - *ሥጋው* - የሚሞት ፣ የሚበሰብስ ፣ ክብር የጎደለው (ሮሜ6፡12፤7፡24)
        - ነፍሱ - የተበላሸ አእምሮ ደግ ማሰብ ያቃተው (ሚክ2፡1፤ሮሜ1፡21 2ቆ43፡14) ምርጫው ሁሉ የተበላሸ ሆነ።
        - መንፈሱ - መልክሙን ክፉውን ፣ የተዋረደውን ከከበረው መለየት ተነሳው።
    - *የመነሻ ሐሳቡ ተበልሻቶአል* - ሰው ምንም እንኳ መልካም እና በጎ ነገሮችን ማድረግ ቢችልም የመነሻ ሐሳቡ ግን የተበላሸ ነው / wrong motive/።ሉቃ10፡27
    - *ወደ እግዚአብሔር የመቅረብ ድፍረቱ ተበላሸ* - እግዚአብሔር ራሱ ሰዎች ወደ እርሱ የሚቀርቡበትን መንገድ በክርስቶስ በኩል አዘጋጀ አንጂ ሰው ግን ፈጽሞ የመቀረብ እና ፊቱ የመቆብ ድፈረቱን አጣ።ዮሐ6፡44፤ሮሜ3፡1-23 2ቆሮ4፡3-4
- አጠቃላይ ጥፋት ያልሆነውስ የቱስ ነው
    - *ምንም ዓይነት መልካምነት በሰው ውስጥ የለም ማለት አይደለም* - በመሆኑም ሰው ክፉውንና ደጉን ማሳየት ይችላል፣ደግ ስራዎችን ማከናውን ይችላል
    - *ሰው ሕሊናውን ሙሉ በሙሉ አጥቶአል ማለት አይለም*- መልካም እና ክፉውን የመለየት አቅሙ ፣ መልካም ግበረገባዊነትን ማራመድ ይችላል።
    - *ሰው ሰው መሆኑ አጥቶአውል ማለት አይደለም* - ሰው ኃጢያትኛ ሆነ እነጂ ሰብአዊ ተፈጥሮውን ግን አላጣም።

- *አጠቃላይ ጥፋት ማለት ሰው ሁሉ የትኛውንም ኃጢያት ይሰራል ማለት አይደለም-* ምክንያቱም ሰዎች በፈቃዳቸው የማይሰሯቸው እና የሚሰሯቸው ስህተቶች አሉአቸው።

✓ አጠቃላይ ጥፋት ያለው እንድምታ -

- ሰዎች እጅጉን ጥፋተኝነት ከተሰማቸው በሕይወታቸው ላይ የሚገለጠውን የእግዚአብሔርን ጸጋ ያደንቃሉ፤ሮሜ 5፡20
- የኃጢያቱን ብዛት እና የእግዚአብሔርን ምህረት ምን ያህል ለእርሱ እንደ ሆነ የተረዳ ሰው ለእግዚአብሔር እጅግ በጣም ብዙ ፍቅር አለው ፤ ሉቃ7፡36-50
- የወንጌል ስብከታችን ፍጹም ምሉዕ አይሆንም የኃጢያትን አጠቃላይ ጥፋት በሰዎች ልጆች ላይ ያደረሰውን ካልሰበክን በመሆኑም የኃጢያትን ተፈጥሮ፣ ጉልበት፣ ስፋት ማሳየቱ ለሰዎች ደህንነት እጅግ ተገቢ ነው።

### *3.3.3 ሦስት የኃጢያት ምልክቶች*

☞ *በዓለም ያለ ክፋት*- ዓለም እና በውስጧ ያለው የሕይወት ዘይቤዋ ፣ የሕይወት እሴቶች እና መንገዶች እጅጉን ክፉ ናቸው። ፤፤ዮሐ15፡18-19፤ 1ዮሐ5፡19

☞ *በሰው ውስጥ ያለ ሽንፈት/ኃጢያት*- በአንዱ አዳም ምክንያት በሰዎች ውስጥ ያለ "የኃጢያተኛ ተፈጥሮ" "የኃጢያት ሕግ/ኃይል" ሁል ጊዜ የምታገለው ነው።1ዮሐ2፡15-16 ገላ5፡17፤ ሮሜ8፡5፤7

☞ *ከዲያብሎስ የሚሰጠን የኃጢያት ግብዣ* - ሰይጣን በክፉው ሥራው እንድንተባበረው የኃጢያት ግብዣዎችን ያቀርብልናል። ጌታን እንደፈተነው በክፉ ይፈትነናል።

## *3.4 የማህበረሰብ ኃጢያት ገጽታዎች*

### *3.4.1 ማህበረሰባዊ ኃጢያቶች*

በዚህ አውድ ለማለት የተፈለገው የአንድ ግሩፕ/ቡድን ፣ ሕዝብ፣ ሕብረተሰብ ከእግዚአብሔር ትእዛዛት የሚቃረንን ስርዓት ተከትለው ሲሄዱ ለማሳየት ነው። ይህም በአሁኑ ዘመን ሰዎች መብታችን ተገፈፈ በሚል መሪ ሐሳብ አድሎ ተደረገበኝም በሚል እሳቤ ሰዎች በህብረት ለራሳቸው የሚቀርጹት ሕግ ነው።እነዚህም አካሔዶች ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር ያጋጩታል ለምሳሌ፡-

❖ የዘር ፖሊሲዎች አንዱ ዘር ከሌላው የበላይነቱን ለማረጋገጥ

❖ ጽንስን የማቋርጥ ፖሊሲ

❖ ጾታዊ የተጽእኖ ፖሊሲ (አንድ ወገን ፆታ የሚወግን)

❖ የሴት ልጆች ግርዛት

❖ የተመሳሳይ ጾታ ጋብቻ

- ❖ የግዳጅ ጋብቻ
- ❖ ከአንድ በላይ ጋብቻ

### *3.4.2 መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ ስለ ማህበረሰባዊ ኃጢያቶች*

✓ *የክፉ ዓለም የኑሮ መርህን አስመልክቶ* :- ሰዎች ለራሳቸው ምቾት የሚያወጧቸው የአንድ ሕብረተሰብ እስቶች፣ልምዶች፣የሕይወት ፍልስፍናዎች (ዮሐ15፡18-19፤ቆላ1፡13፤ ያዕ1፡27 1ዮሐ2፡15-17)

✓ *የምድር ገዢዎች እና ባልስጣናትን አስመልክቶ* :- በርግጥ ይህ ቃል ለክፉ መንፈሳዊ ሰራዊትም አገልግሎት ውሎአል። ይሁን እንጂ በዚህ አውድ ለማሳየት የተፈለገው የምድር ገዢዎችን ነው። ኢኮኖሚውን፣ ባህሉን ፣ ፓለቲካውን ፣ ሃይማኖታዊ ተቋማትን በበላይነት ስለ ሚመሩት ነው። ከወደቀው ሰው መካከል ናቸው በመሆኑ ኃጢያተኛ ናቸው ፤ ስሜታቸው ፣ እውቀታቸው ፣ ምክራቸው ሁሉ ፈጽሞ የተበላሸ ነው።

### *3.4.3 በማህበረሰብ የተወገዙ ኃጢያቶችን መለየት/ማወቅ አለመቻል*

ሰዎች የማህብረሰብ ኃጢያት መለየት የሚያቅታቸው ምክንያት

1. ግለሰቦች የግሩፑን ውሳኔ በግል ተጠያቂ እንደማይሆኑ ስለሚያስቡ
2. ልባቸውን አስፍተው ጉዳዩን ለመቀበል ስለሚዘጋጁ
3. የግሩፑን ድርጊት እንደ ራሳቸው እርምጃ አድረገው ስለማያስቡት
4. የማህበረሰቡ እሴቶች ግለሰቡን ሲጎዱት በቀጥታና በግልጽ ባለመሆኑ ምክንያት
5. ጉዳዮን ከሕብረሰብ ጥቀም አንጻር ብቻ ስለሚመለከቱ

### *3.4.4 የማህበረሰብን ኃጢያቶችን ማረም*

የህብረተሰብን ኃጢያት ማረም የሚቻልበት መንገች

1. በወንጌል - ወንጌል ሰውን ይለውጣል ፣ አዲስ ፍጥረት ያደረጋል
2. የማህበረሰብን ማዋቅራዊ ህጎችንና ደንቦች በማሻሻል
   - ✓ መጽሐፍ ቅዱሳዊ በሆኑ መርሆች ህብረተሰብን በመቅረጽ

# *4. ተያያዥነት ያላቸው አመለካከቶች እና ሐሳቦች*

### *4.1 ኢ- ክርስቲያናዊ አመለካከቶች*


4.1.1 በአንድ አምላክ መኖር ብቻ የሚያምኑ እምነቶች ስለ ኃጢያት ያላቸው አመለካከት

- ✓ በዚህ ርዕስ ሥር የሚጠቀሱ እምነቶች አይሁዳዊነት፣ እስልምና እና ክርስትና ነው
    - ○ ለሙስሊም - ኃጢያት የአላህን ህግጋት መተላለፍ ነው፤
    - ○ ለአይሁድ - ኃጢያት የእግዚአብሔር ሕግ በሙሴ በኩል የተሰጡትን እና የሽማግሌዎችን ወግ መተላለፍ ነው፤
    - ○ ለክርስቲያን - ኢየሱስ ክርስቶስን ጌታ እና አዳኝ አድርጎ አለመቀበል ነው።

4.1.2 የሌሎች ሃይማኖቶች አመለካከት ኃጢያትን አስመልክቶ

- ✓ ሂንዱዊዝም
    - ○ ሰው ኃጢያተኛ አይደለም፣መሰረታዊው እውነት ግን ሰው መልካም ነው
    - ○ ክፉ ሊሰራ ይችላል ነገር ግን እርሱ ክፉ መሆኖ አይችል
    - ○ በኑሮው የሚያጋጥመች ችግር ከዚህ በፊት የሰራው የክፉ ስራው ውጤት ነው
    - ○ ቢሆንም ክፉ/መጥፎ የሚባለው ነገር ሐቅ አይደለም ነገር በእርግጥም እውን መኖሪያ ባለሆነቸው በዚህች ዓለም ማይታው ነገር ነው።
    - ○ በእውነትም ኃጢያት ካለ እርሱም አለማወቅ ነው፤ ትልቁም አለማወቅ ይህችን ዓለም እውነተኛ አድርጎ ማሰብ ነው
- ✓ ቡዲዝም
    - ○ ችግር/መከራ አለ
    - ○ የመከራ ሁሉ ምንጭ የሰዎች ፍላጎት ነው
    - ○ መከራ የሚጠፋው ፍላጎት ሲሞት/ሲጠፋ ብቻ ነው
    - ○ መከራን ለማጥፋት ደገሞ ቡዲዚም የሚያምንባቸውን ሰምንት መንገዶች በመከተል ነው
        1. ትክክለኛ እይታ
        2. ትክክለኛ ተመስጦ
        3. ትክክለኝ ንግግር
        4. ትክክለኛ ግንኙነት
        5. ትክክለኛ የሕይወት መንገድ
        6. ትክክለኛ አቅም
        7. ትክክለና ግንዛቤ
        8. ትክክለኛ ትኩረት በማድረግ ሰው መከራን ሊያመጡ የሚችሉ ፍላጎቶቹን መግደል ይችላል።

- ✓ ኮንፊሺዝም
    - ኮንፊሽን እምነት ሳይሆን የግብረከብነት መርህን የሚከተል ነው
    - ሰው በመሰረቱ መልካም ነው
    - ምናልባት ሰው ክፉ ከሰራ ከራሱ ተፈጥሮ ውጪ እየተራመደ ነው
    - ትልቁ እና ወርቃማው ሕግ “በአንተ ላይ እንዲሆን የማትፈቅደውን ጉዳይ በሌሎች ላይ አታዳርግ”
    - ኃጢያት ማለት ከሌሎች ጋር አግባብነት የጎደለው ግንኙነት ማድረግ ማለት ነው።
- ✓ ታኦይዝም
    - ይን እና ያንግ በሚባሉ የኃይል መርሆች ላይ ተመሰረተ ነው
        - ይን- ኔጋቲቭ ሲሆን ደካማና የሴትን ኃይል ገላጭ ነው
        - ያንግ ደግሞ ፖዘቲቭ ሲሆን ጠንካራ እና የወንድን ኃይል ገላጭ ነው
    - ክፋት የሚከሰተው የእነዚህ ሁለት ኃይል እኩል በማይመጣበት ጊዜ/ ወቅት ነው



TAOISM

4.1.3 አለማዊ አመለካከት

- ✓ የዝገምተኛ ሂደት አመለካከት ያላቸው
    - ክፉ ሊኖር የሚችለው ሰው የእድገት ሂደቱን ስላልጨረ/ስላላጠናቀቀ ነው።
- ✓ ስነ ልቦናዊያን አመለካከት ያላቸው
    - ክፋት ሰዎች ከውጣቸው የሚያወጡት ቅሰፈታዊ ድርጊት ነው፤ ምንልባትም ከዙሪያው ከሚፈጠሩ ነገሮች እራሱን ለመጠበቅ ለማዳን …ወዘተ
    - ሰው በሰዙሪያው ካሉት ከወላጆች ከቤተሰቡ ጀምሮ እስከ ማህብረስብ ድረስ ያለ ድምር ውጤት ነው። በመሆኑም አንድ ሰው ያለው ባህሪ የራሱ ሳይሆን ከዙሪያው ካሉት ማህበረሰብ ያገኘው ነው።
- ✓ ኤዚስቴሺያን አመለካከት ያላቸው

- ○ ክፉ መኖሩን ይቀበላሉ በመሆኑም የክፉውን ተፈጥሮ ያብራራሉ ነገር ግን የክፋት መንስዔ ከየት እንደሆነ ግን አይመልሱም
- ○ ሰው በራሱ ለችግሮቹ መፍትሔ ይሰጣል ብለው ያምናሉ
- ○ ሰው ከችግሩ ነጻ ሊሆን የሚችለው በሕይወቱ ዓላማ ላይ ሲያተኩር ነው

## *4.2 ከኃጢያት ጋር የሚያያዙ ሐሳቦች*

### 4.2.1 ይቅር የማይባሉ ኃጢያቶች - መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክፍሎች

- ✓ ማቴ12፡31-32 - መንፈስ ቅዱስን መሳደብ
- ✓ ዕብ6፡4-6 - ክርስቶስ ኢየሱስን እንደገና መስቀል
- ✓ ዕብ10፡26-29 - በኃጢያት ጸንቶ መኖር
- ✓ 1ዮሐ5፡16-17 - ለሞት የሚያደርስ ኃጢያት

### 4.2.2 ይቅር የማይባሉ ኃጢያቶች ባህሪ

- ✓ መንፈስ ቅዱስን መሳደብ መንፈስ ቅዱስን ከማሳዘን እጅግ በጣም የተለየ ነው።ኤፌ4፡30
- ✓ መንፈስ ቅዱስን መሳደብ
    - ☞ የእግዚአብሔርን ሥራ በመንፈስ ቅዱስ የአጋንንት ሥራ አድርጎ ማየትእና መራመድ
    - ☞ መንፈስ ቅዱስ የሚሰራውን የድህነት ሥራን ኢየሱስ ክርስቶስን እንድ አዳኝ አድርጎ ለመቀበል ፍቃደኛ አለመሆን
    - ☞ በመንፈስ ቅዱስ ቦታ ለመሆን መፈለግ (መለኮት ለመሆን የሚደረግ ጥረት)
- ✓ በፍጹም በቃደኝነት እና እወቀት ላይ ስራዬ ተብሎ የሚሰራ ኃጢያት
- ✓ ፍጹም ግልጽ እና የሚታይ የእግዚአብሔር መገለጥ ላይ የሚሰራ ኃጢያት

### 4.2.3 የኃጢያት ደረጃ

- ✓ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የኃጢያት ትልቅ እና ትንሽ የለም። ይኼኛው ኃጢያት ከዚያኛው ኃጢያት ይበልጣል አይለንም። ይልቁን እንደ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አስተምህሮ ከሆነ ወደ ሴት ያየ እና የተመኘ በልቡ አመንዝሮአል ስለሆነም ፍርድ ይገባዋል ብሎአል።
- ✓ ነገር ግን በአብዛኛው በሰዉ ዘንድ የተለመደው ኃጢያት በሚያደርሰው ውጤት ስንመዝን እንገኛለን፤ ሰው ከመግደል እና ከመዋሸት ትልቁ ኃጢያት ሰው መግደል ነው። ምክንያቱም ሰው መግደል ውጤቱ ከበዳ ስለሆነ።
- ✓ በእግዚአብሔር ዘንድ ግን የሰው መነሻ ሐሳብ ይለካል እንጂ ውጤቱ አይለካልም።

- ✓ የኃጢያት ልዩነት ሳይሆን የኃጢያተኛ ልዩነት አለ። በመሆኑም ኃጢያት በራሱ ሳይሆን የሚለካው በኃጢያተኞች ኃጢያተኝነት ልክ ነው።
    1. ይቅር የማይበሉ ሰዎች አሉ ፤ ምክንያቱም የሰሩት ኃጢያት ይቅር የማያስብላቸው በመሆኑ
    2. በሉቃ12፡47-48 መሰረት ደግሞ ሰው እያወቀ ሲያጠፋ የበለጠ ከባድ ኃጢያተኛ ይሆናል
- ✓ በዚህ ሃሳብ መሰረት ተጨማሪ ጥቅሶችን ልብ ማለት ይቻላል።
    - ዘፍ6፡11-12 – “ምድርም በእግዚአብሔር ፊት ተበላሸች ምድርም ግፍን ተሞላች። እግዚአብሔርም ምድርን አየ፥ እነሆም ተበላሸች ሥጋን የለበሰ ሁሉ በምድር ላይ መንገዱን አበላሽቶ ነበርና።” ምድር በሙሉ ክፉ ስራ በመስራታቸው “ተሞላች” ይላል። የሰዎች ክፋት ምን ያህል ከፍ እንዳለ ለማሳየት።
    - ዘፍ15፡16 – “በአራተኛው ትውልድ ግን ወደዚህ ይመለሳሉ የአሞራውያን ኃጢአት ገና አልተፈጸመምና።” የክፋታቸው ብዛት ጽዋ አልሞላም ገና ነው። መለኪያው የኃጢያቱ ዓይነት ሳይሆን የኃጢያተኞቹ ተግባር ነበር።
    - ማቴ24፡12 – “ከዓመፃም ብዛት የተነሣ የብዙ ሰዎች ፍቅር ትቀዘቅዛለች።” የሚለካው የዓመጽ ብዛት የኃጢያተኞቹ የክፋት መጠን እንጂ የኃጢያቱ ዓይነት አይደለም።
- ✓ የኃጢያት መለኪያ/የሚዛን መሰረት
    1. የሰዎች እውቀት መጠን ፡- ብዙ አወቆ ያጠፋ በብዙ ይቀጣል፣ ትንሽ አውቆ ያጠፋ በትንሹ ይቀጣል።
    2. የድሪጊት መነሸ ሐሳብ / Motive/ ፡- የኃጢያቱ ዓይነት ሳይሆን ድርጊቱን ለመፈፀም የተነሳንበት የውስጥ ስሜት በጌታ ዘንድ ይመዘናል። ለዚህም በቡሉይ ኪዳን የተደነገጉ ሕጎችም ነበሩ። ዘኍ35፡16-28 ፤ ዘሌዋ4፡2

### 4.2.4 ፈተና እና ኃጢያት

ማንኛውም ክርስቲያን እንደ ሚፈተን መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። በመሆኑም እግዚአብሔር መንፈሳዊ ሕይወታችንን ሊያጠንክርበት ይጠቀመዋል። ያዕ1፡2-4 ፈተና በራሱ ኃጢያት አይደለም። ጌታችን ከኃጢያት በስተቀር በነገር ሁሉ እንደ እኛ ተፈትኖአል። ዕብ4፡15

- ✓ የፈተና ምንጮች
    - ከውጭ ፡- ይህ ከክፉዎች አሊያም ከዲያብሎስ ወደ እኛ የሚመጡ የኃጢያት ግብዣዎች ናቸው።
    - ከውስጥ ፡- ይህ ከገዛ ራሳችን ምኞት እና መሻት በመነሳት የምንፈተነው።
- ✓ የፈተና ደረጃዎች
    - ደረጃ አንድ- ከውጭ ክፉ ሐሳቦች እና ምኞቶች ከሰይጣን ወደ ልባችን ሲመጣ።
    - ደረጃ ሁለት - ወደ ልባችን በሚመጣው ክፉ ሐሳብ ውስጣችን ሲስማማ እና ሲደሰት።
    - ደረጃ ሶስት - በቃዳችን ወደ ልባችን ለገባው ክፉ ሐሳብ ሲሰጥ።

## *4.3 የሰው ፍጻሜ*

### *4.3.1 የታደው የሰው ልጆች ተስፋ (1ቆሮ15 ፤ ራዕ21፤22)*

❖ ***መንግሰተ ሰማይ***

- መንገሰተ ሰማይ ምን ትመስላለች? (ዮሐ14፡1-3)
- በዮሐንስ ራዕይ ገለጣ መሰረት 21ኛው እና 22ኛው ምዕራፍ
    - ☞ መልካም ገጽታዋን - በከበሩ ዱንጋዮች ይገለጠዋል
    - ☞ የእግዚአብሔር ዙፋን መገኛ ናት
    - ☞ የበጉ መቀመጫ ናት
    - ☞ ያመኑትም ዋና ተግባራቸው እግዚአብሔርን ማወደስና ማክበር ብቻ ነው።
    - ☞ የዳነው ሰው ሁናቴ በመንግሰተ ሰማይ
        - ✓ ፍጹም መደህንነት
        - ✓ ፍጹም ቅዱስ
        - ✓ ፍጹም የከበረ ሰውነት
        - ✓ ፍጹም ደስታ
        - ✓ ፍጹም እግዚአብሔርን ወራሽ ነው።
    - ☞ በመሆኑም በመንግሰተ ሰማይ የማይገኘው
        - ✓ ኃጢያት ፍጽሞ የለም
        - ✓ ሞትና የሞት ፍርሃት የለም
        - ✓ ፈጽሞ ጋብቻ የለም (ማቴ22፡29-30)

❖ የክብር ስፍራ

- ☞ በክርስቶስ ወንጌል የከበሩቱ የሚሰበሰቡበት ስፍራ (ሮሜ8፡30 5፡2  8፡18)
    - ✓ መንገስተ ሰማይ እጅግ ውብ ከተማ ናት! የእግዚአብሔር ክብር እና ውበት የታየው ፈጠረው ፍጥረት ነው። (መዝ19፡1-4)

- ❖ ሽልማት
    - ☞ ማቴ5፡12 - "የዋሆች ብፁዓን ናቸው፥ ምድርን ይወርሳሉና።"
    - ☞ ሉቃ6፡23 – "እነሆ፥ <u>ዋጋችሁ በሰማይ ታላቅ</u> ነውና በዚያን ቀን ደስ ይበላችሁ ዝለሉም፤ አባቶቻቸው ነቢያትን እንዲህ ያደርጉባቸው ነበርና።"
    - ☞ ማቴ 6፡1-4 - "ለሰዎች ትታዩ ዘንድ ምጽዋታችሁን በፊታቸው እንዳታደርጉ ተጠንቀቁ፤ ያለዚያ <u>*በሰማያት ባለው አባታችሁ ዘንድ ዋጋ የላችሁም*</u>፡እንግዲህ ምጽዋት ስታደርግ፥ ግብዞች በሰው ዘንድ ሊከበሩ በምኩራብ በመንገድም እንደሚያደርጉ በፊትህ መለከት አታስነፋ፤ እውነት እላችኋለሁ፥ ዋጋቸውን ተቀብለዋል።አንተ ግን ምጽዋት ስታደርግ ምጽዋትህ በስውር እንዲሆን ቀኝህ የምትሠራውን ግራህ አትወቅ፤ በስውር የሚያይ <u>*አባትህም በግልጥ*</u> ይከፍልሃል።"
    - ☞ ማቴ 10፡42 - "ማንም ከእነዚህ ከታናናሾቹ ለአንዱ ቀዝቃዛ ጽዋ ውኃ ብቻ በደቀ መዝሙር ስም የሚያጠጣ፥ እውነት እላችኋለሁ፥ <u>ዋጋው አይጠፋበትም</u>።"
    - ☞ ሉቃ6፡35 - "ነገር ግን ጠላቶቻችሁን ውደዱ፤ መልካም አድርጉ፤ ምንም ተስፋ ሳታደርጉም አበድሩ፥ <u>ዋጋችሁም ታላቅ ይሆናል</u>፥ የልዑልም ልጆች ትሆናላችሁ፥ እርሱ ለማያመሰግኑ ለክፉዎችም ቸር ነውና።"
    - ☞ ዕብ11፡6 - "ያለ እምነትም ደስ ማሰኘት አይቻልም፤ ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔር እንዳለ <u>ለሚፈልጉትም ዋጋ</u> እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና።"
    - ☞ ያዕ1፡12 - "በፈተና የሚጸና ሰው የተባረከ ነው፤ ከተፈተነ በኋላ ለሚወዱት ተስፋ ስለ እርሱ የሰጣቸውን የሕይወትን <u>አክሊል ይቀበላልና።"</u>
    - ☞ ራዕ22፡12 - "እነሆ፥ በቶሎ እመጣለሁ፥ ለእያንዳንዱም እንደ <u>ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ</u> ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ።"

### *ሰማያዊ ሽልማት ለድል ነሺዎች*

- 🕊 ራዕ2፡7 –"ድል ለነሣው በእግዚአብሔር <u>ገነት ካለው ከሕይወት ዛፍ</u> እንዲበላ እሰጠዋለሁ።"
- 🕊 ራዕ2፡11 – "ድል የነሣው በሁለተኛው <u>*ሞት አይጐዳም።"*</u>
- 🕊 ራዕ2፡17 – "ድል ለነሣው <u>*ከተሰወረ መና*</u> እሰጠዋለሁ፥ <u>*ነጭ ድንጋይንም*</u> እሰጠዋለሁ፥ በድንጋዩም ላይ ከተቀበለው በቀር አንድ ስንኳ የሚያውቀው የሌለ አዲስ ስም ተጽፎአል።"

- ራዕ2፡26-28 – "ድል ለነሣውና እስከ መጨረሻም ሥራዬን ለጠበቀው እኔ ደግሞ ከአባቴ እንደ ተቀበልሁ *በአሕዛብ ላይ ሥልጣንን እሰጠዋለሁ፥* በብረትም በትር ይገዛቸዋል፥ እንደ ሸክላ ዕቃም ይቀጠቀጣሉ፤"
- ራዕ 3፡5 – "ድል የነሣው እንዲሁ በነጭ ልብስ ይጐናጸፋል፥ ስሙንም ከሕይወት መጽሐፍ አልደመስስም፥ በአባቴና በመላእክቱም ፊት ለስሙ እመሰክርለታለሁ።"
- ራዕ 3፡12 – "ድል የነሣው *በአምላኬ መቅደስ ዓምድ* እንዲሆን አደርገዋለሁ፥ ወደ ፊትም ከዚያ ከቶ አይወጣም፤ የአምላኬን ስምና የአምላኬን ከተማ ስም፥ ማለት ከሰማይ ከአምላኬ ዘንድ የምትወርደውን *አዲሲቱን ኢየሩሳሌምን፥ አዲሱንም ስሜን* በእርሱ ላይ እጽፋለሁ።"
- ራዕ 3፡21 - "እኔ ደግሞ ድል እንደ ነሣሁ ከአባቴም ጋር በዙፋኑ ላይ እንደተቀመጥሁ፥ ድል ለነሣው *ከእኔ ጋር በዙፋኔ ላይ ይቀመጥ* ዘንድ እሰጠዋለሁ።"

### 4.3.2 የአመጸኛ ሰዎች የወደ ፊት እጣፈንታ

- ✓ በራዕይ 21፡8 መሰረት የአመጸኞች የመጨረሻ ፍጻሜ የሆነውን የእሳት ባህር በግልጽ ያሳየናል።
- ✓ የመጨረሻ ፍርድ የሚያገኙበት እውነት ተገልጦላቸው ለእውነት ባለ መታዘዛቸው ምክንያት ቅጣት ወደ ሚቀበሉበት ስፍራ ይገባሉ። ማቴ7፡23 25፡12
- ✓ ከእግዚአብሔር ጋር ለዘላለም ይለያሉ። ማቴ 25፡30
- ✓ የሲዖል ገጽታ (ማቴ25፡30 ፤ ራዕ20፡15 ፤ ራዕ20፡10 ማር9፡48)

## 5. ማጠቃለያ

በእግዚአብሔር መልክ እና አምሳል ተፈጠረን በአንዴ በአዳም ኃጢያት ምክንያት ለሁላችንም ክፉ ደረሰን። ይኸውም ከእግዚአብሔር ፍጹም ሕብረት መለየት፣ከተሰጠን የሕይወት ደረጃ መውረዳ እና ኃጢያተኛ መሆን ፣ በርእግማን ስር መሆን መጣ ነገር ግን እግዚአብሔር በክርስቶስ ባደረገልን መልካም ስራ ሕይወት እና ክብር እጅግ በብዙ እጥፍ ተመለሰለን። የዘላለም ሕይወት እና የዘለላም ክብር ለእኛ ሆነ። ስለዚህ ይህንን እውነት መስበክ ማስተማር ለሌሎች ይጠበቅብናል። እግዚአብሔርም ስላደረገልን መልካም ነገር ልናመሰግነው ይገባል።

ክብር ሁሉ ለዘላለሙ ጌታ ለኢየሱስ ክርስቶስ ይሁን!